# ግንቦት 20ና የቀለም ዘመዴ

ዝም ብዬ ስኖር ስድብ ሳይሰለቸኝ
ምገላገልበት አመራጭ ሳይኖረኝ
እኔ በኔነቴ ራሴን ሲቀፈኝ

ምንአይነት አገር ላይ እንደምን ፈጠረኝ
ሰው ሰለጠቆረ ሐጢያት በዝቶበት
መተፋት መገፋት መናቁ ሰልችቶት
ራሱን ቢገልስ ከቶ ምንአለበት

ሳቄን ወደለቅሶ እየለወጡብኝ
ለቅሶዬን ወደሳቅ እየቀየሩብኝ
የጥቁር እንግድነት ዜግነት ሰጥተውኝ
በኔነቴ ብዙ ፤ ብዙ ሲያፌዙብኝ
እንደዚህ መሆኔ  ፍጥረቴ አስገረመኝ

የዚም የዚያም  ችግር ተዳምሮ በዛና
አብዮት አክሎ ፍንዳታ ሆነና
የኔ ቢጤ ጥቁር ዙፋን ላይ ወጣና
የፍየል ወጠጤ በሚል ብሩህ ዜማ
አረደው አገሩን አለም እሰኪሰማ

የቀለም ዘመዴ በወፍራም ሲገርመኝ
ፍጥረቴ የሰጠኝ ስድብም ሳያነሰኝ
ባለፍኩ በገደምኩበት በቃ እኔ እርሱን ሆንኩኝ
አገር በላው መንጌ ድርብ አሰደበኝ

በጣሙን ይገርማል የጊዜ ምህዋር
የቀለም ዘመዴ በሸንፈት ሲዘረር
ዚምባብዌ ተጉዞ ገባ ያለችግር
የኔ እጣ ፈንታ ግን በይደር ውሎ አድሮ
ግንቦት 20 መጣ ለፍርድ ቀጠሮ

ስንጠብቅ ታጋዩን ሁሉም ተሰብስበን
ሰው በቀለም ብሄር ማንቋሸሽ መበደል
ከዛሬ ጀምሮ ገብተዋል ወደ ገደል
አለና ቆራጡ እንቀጩን ነገረን

ተብላ እንዳልነበር የብሄር አስር ቤት
ሀገሬ ኢትዮጲያ ሰራች የእኩል ቤት
በተፈጥረኩበት ሀገር ቀላወጭ ነበረኩኝ

ዛሬ ግን ያለፈርሀት በሰላም አደርኩኝ
የራሴን እድል በራሴ አደረኩኝ
ማንም ምንም ቢል እኔ ምን ቸገረኝ
እኔ በኔነቴ በጣም ደስተኛ ነኝ
ሥለኔ ምወስነው እኔው እራሴ ነኝ

ይሄም ታሪክ ይባል በእወነት ነውና
እራሴን መሆኔ ተረጋግጧልና

አ.ተ.ጥሩነህ